Made for minds.



# የዶይቸ ቬለ (DW) የጀርመንኛ ቋንቋ ትምህርት

ዶይቸ ቬለ (DW) በኦንላይን በነፃ በሚሰጠው የቋንቋ ትምህርት አገልግሎት የጀርመንን ባህልና ቋንቋን ይወቁ ፡፡

ዶይቸ ቬለ (DW) ላላፉት 60 ዓመታት በዘመናዊ ዘዴ የተለያዩ የጀርመንኛ ቋንቋ ትምህርቶችን ሲሠጥ ቆይቷል ፡፡ በሁለትዮሽ ቋንቋ የሚሰጡት ትምህርቶች ለጀማሪዎች ምቹ ናቸው ፡፡ መለስተኛ የጀርመንኛ ቋንቋ ችሎታ ያላቸው (ጀማሪ ያልሆኑ ተማሪዎች) ደግሞ ልዩ በሆኑት አጫጭር ድራማዎች አማካኝነት ችሎታቸውን ማዳበር ይችላሉ ፡፡ የቋንቋ ትምህርቱ ጽሁፍን ማንበብ ፣የድምጽ ቀረጻዎችን መስማት ወይም የምስል ቪዲዮዎችን ማየት ለሚፈልጉ ሁሉ እንደየፍላጎታቸው ተዘጋጅቷል ፡፡ያለ ኢንተርኔት አቅርቦት (ኦፍላይን) ትምህርቶችን ለመከታተል ከፈለጉም የትምህርት አሰጣጡን ኮምፒውተርዎ ላይ መገልበጥ ይችላሉ ፡፡

dw.com/learngerman/amharic

## Audiotrainer
### ባለ100 ክፍሎች የቃላት መማሪያ




A1 A2 B1 B2 C1 C2

**ቋንቋዎች**
ቻይንኛ ፣እንግሊዘኛ ፣ፈረንሳይኛ ፣ፖርቱጋሊኛ ፣ሩሲኛ እና ስፓኒሽኛ

**መሳሪያዎች**
የመልመጃ ወረቀቶች እና የመልመጃ መጻህፍትን (ከwww.book2.de መገዛት ይቻላል)

የቃላት ድምፅ አወጣጥን ለማሻሻል የሚያስችሉትን መሠረታዊ ዘዴዎች በAudiotrainer አማካኝነት ሊማሩ ይችላሉ ፡ ፡ ባለ 100 ክፍሎቹ የቃላት መማሪያ በጀርመን ስላለው የኑሮ ሁኔታ በሚገባ ለመረዳት ይጠቅምዎታል።

የቋንቋ ትምህርቶቹ በአጠቃላይ በኦንላይን ሊያገኟቸው ወይም እንደ MP3 ሊገለብጡዋቸው ይቻላል ፡ ፡ አልያም ሁሉንም የትምህርት ክፍሎች በፖድካስት እንዲደርስዎ ሊያዙ ይችላሉ ፡ ፡Audiotrainer በራስዎ ፍጥነት ችሎታዎን እንዲያዳብሩ ይረዳዎታል ፡ ፡

dw.com/learngerman/audiotrainer

## Deutsch – warum nicht?
### መደበኛ በድምጽ የሚሰጥ የቋንቋ ትምህርት




A1 A2 B1 B2 C1 C2

**ቋንቋዎች**
ጀርመንኛ ፣እንግሊዘኛ እና ሌሎች 26 ቋንቋዎች

**መሳሪያዎች**
ጽሁፎች እና የሚታተሙ የመልመጃ ደብተሮች

Deutsch – warum nicht? የአንድሪያስን ታሪክ በአራት ተከታታይ ክፍል ያወጋል ፡ ፡ ወጣቱ በአንድ ሆቴል በር ከፋች ሆኖ የሚሰራ ተማሪ ነው ፡ ፡

እያንዳንዱ ተከታታይ ትምህርት ባለ 26 መገልበጥ (ዳውንሎድ) ሊደረግ የሚችል ክፍሎች አሉት። እነሱም ውይይቶችን ፣ የሰዋሰው ማብራሪያ ፣ መልመጃ እና የድምጽ መዝገብን ያካተቱ ናቸው ፡ ፡ ትምህርቱ በሁለት ቋንቋ የሚሰጥ ሲሆን ጀርመንኛን ዘና ብለው በሚያውቁት ቋንቋ ይማራሉ። ትምህርቱ በ28 የተለያዩ ቋንቋዎች ያገኙታል ፡ ፡

dw.com/learngerman/amharic/warumnicht

# Deutsch Interaktiv

## እራስን በራስ የማስተማር የኦንላይን ትምህርት




A1 A2 B1 B2 C1 C2

**ቋንቋዎች**
ጀርመንኛ ፣ እንግሊዘኛ ፣ሩስኛ

**መሳሪያዎች**
አሳታፊ መልመጃዎች ፣ መዝገበ ቃላት ፣ የሰዋሰው ማገዣዎች ፣ መልመጃ ወረቀቶች እና የጥናት መረጃዎች ፡፡

Deutsch Interaktiv ብዛት ያላቸውን መልመጃዎች ፣ የድምጽ መዛግብት ፣ቪድዮዎች እና ፎቶዎችን የያዘ ሲሆን ይህም መማርን አስደሳች ያደርገዋል ፡፡ ከ7000 በላይ ቃላት ያሉት መዝገበ ቃላት እና የሰዋሰው ጠቅላላ መግለጫ እንዲሁም ቃላትና የድምጽ አወጣጥ መማሪያ ዘዴዎች ትምህርቱን ይበልጥ ቀላል ያደርጋሉ ፡ ፡ስለሆነም የግል የሆነ የመማርያ ማህደር እንዲኖርዎ በነጻ ይመዝገቡ ፡ ፡ፕሮግራሙ ውጤትዎን ይመዘግባል ፤ ትምህርቱንም እንዴት መቀጠል እንዳለብዎ ይመራዎታል ፡፡ በዚህ መልኩ ፤ የሚመችዎትን የመማርያ ጊዜ መምረጥ ይችላሉ ፡፡

dw.com/learngerman/amharic/deutschinteraktiv

# Jojo sucht das Glück

## ጀርመንኛ መማሪያ አጫጭር ድራማዎች (ቴሌኖቬላ)




A1 A2 B1 B2 C1 C2

**ቋንቋዎች**
ጀርመንኛ

**መሳሪያዎች**
አሳታፊ መልመጃዎች ፣ ከቃላት መርጃ ያላቸው ጽሁፎች ፣የመልመጃ ጽሁፍ እና ለመምህራን የሚረዱ ጠቃሚ ሃሳቦች ፣ የኮምፒውተር ምስለ-ግድግዳ እና የጥሪ ድምጾች ፡፡

በJojo sucht das Glück ጀርመንኛን ልዩ በሆነ መንገድ ይማሩ ፡፡ እያንዳንዳቸው 33 ክፍሎች ያሏቸው ሶስት ምራፎች ፤በአሳታፊ መልመጃዎቻቸው የቋንቋ ክህሎትዎን በቀላልና አስደሳች በሆነ መንገድ እንዲያሻሽሉ ይረዳዎታል ፡ ፡ ጀርመንኛ የፍቅር ቋንቋ መሆን እንደሚችል ማን ገምቶ ነበር ?

ብራዚላዊቷ ዮዮን ደስታን ፣ ህይወትን እና ፍቅርን በአዲስ ከተማዎ ኮሎኝ ስትፈልግ ይተዋወቋት!

dw.com/jojo




Available on the
App Store

ANDROID APP ON
Google play

Deutsche Welle | DW Akademie
Bildungsprogramme
53110 Bonn | Germany

bildung@dw.com
© Deutsche Welle 2015

dw.com/deutschlernen